52

8/10/2008

740/2013

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Housing

ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ
<u>ከ/ል/ቤ/ሚ/ር</u>

ጉዳዩ፡ <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ</u>

በየሥራ ክፍሉ ለሚለሙ ሶፍትዌሮች ማረጋገጫ ለመስጠት የተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 52/2008" ሆኖ ከሚያዝያ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሚኒ ካቢኔ የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉና እንድታስፈጽሙ የጸደቀ 1 ጥራዝ መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እያስገነዘብኩ በግልባጩ የመዘገበላችሁ ቢሮወችና ጽ/ቤቶችም በመመሪያው መሠረት እንድትፈጽሙ አስታውቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

**ግልባጭ**

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶች ልማት ዘርፍ)
- ሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ስራ አመራር ቢሮ
- ፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ
- ኮርፖሬትና ሀብት ሥራ አመራር ቢሮ
- ከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ
- መኖሪያ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ
- ከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ቢሮ
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ
- የሚኒስትሩ አማካሪ ቡድን ጽ/ቤት
- ፌዴራል የተቀናጀ የመሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ልማታዊ ኮሚኒኬሽንና ሕዝብ ተሳትፎ ጽ/ቤት
- የፌዴራል የመንግሥት ሕንጻዎች ኮንስትራክሽንና አስተዳደር ቢሮ
- ኦዲት መምሪያ
- ለሕግ መምሪያ

<u>ከ/ል/ቤ/ሚ/ር</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# በየሥራ ክፍሉ ለሚለሙ ሶፍትዌሮች ማረጋገጫ ለመስጠት የተዘጋጀ መመሪያ ቁጥር 740/2013

ሚያዝያ/ 2008

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

**መግቢያ**

በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የዘርፉን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ቴክኖሎጂ ግብአቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ የቴክኖሎጂ ግብአቶች በዘርፉ ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ተደራሽነት ያለው አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት እና ልማታዊ መልካም አስተዳደር ለማስፈን ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ሥራዎች የሚያመነጯቸውን መረጃዎች በኢ.ኮ.ቴ ለማገዝ የሚረዱ መሠረተ-ልማቶችን ለመገንባት፣ የመረጃዎቹን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ መረጃዎቹን ተደራሽ ለማድረግ እና የኢ.ኮ.ቴ. አቅም ለመገንባት የሚያስችል ስትራቴጂ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ ተቋማት የሚያመነጯቸውን የተለያዩ መረጃዎች በአግባቡ ለመያዝ፣ ለመተንተን፣ በፍጥነት ለተጠቃሚ ተደራሽ ለማድረግና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የኢ.ኮ.ቴ. ስትራቴጂ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህንን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ መመሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስር በሚገኙ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት እንዲለሙ የሚፈልጓቸው ሶፍትዌሮች በዘርፉ ያለውን የሀብት ውስንነት በአግባቡ ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚለሙት ሶፍትዌሮች እርስ በእርስ መናበብ የሚችሉ፣ የሀብት ውስንነትን ታሳቢ ያደረጉ፣ ተደጋጋሚ ያልሆኑ፣ ወቅታዊና ዘመናዊ የሆኑ ለማድረግ ይህንን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በየሥራ ክፍሉ ለሚለሙ ሶፍትዌሮች ማረጋገጫ ለመስጠት የተዘጋጀ መመሪያ ቁጥር 740/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"፡- ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

2) "ተጠሪ ተቋማት"፦ ማለት ተጠሪነታቸው ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የሆነ ወደፊትም ተጠሪ ሊሆኑ የሚችሉ ተቋማትን ያጠቃልላል።

3) "ኢ.ቴ.ዳ.ል.ቢ."፦ ማለት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ ነው።

4) "ኢ.ኮ.ቴ."፦ ማለት ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው።

5) "ሰው"፦ ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕጋዊ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

6) "ሶፍትዌር"፦ ማለት የመረጃ ስርዓት መዘወሪያ ነው።

7) "ቢሮዎች"፡ ማለት በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስር በቢሮ ደረጃ ተቋቁመው የሚገኙትን ነው።

8) "ጽ/ቤቶች"፡ ማለት በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስር በጽ/ቤት ደረጃ ተቋቁመው የሚገኙትን ነው።

9) "ሦስተኛ ወገን"፦ ማለት በጨረታ ወይም በህጋዊ ስምምነት ተመርጦ ሶፍትዌሩን የሚያለማ ድርጅት ነው።

10) "ማረጋገጫ"፦ ማለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ሶፍትዌር ለማልማት ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚሰጣቸው ፍቃድ ነው።

11) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተጻፈው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

### 3. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስር የሚገኙ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ሶፍትዌሮችን በውስጥ አቅምም ሆነ በሶስተኛ ወገን ለማልማት ወይንም ለማስለማት በሚጠይቁበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል።

### 4. የመመሪያው ዓላማ

1) በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስር የሚገኙ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ሶፍትዌሮችን በሚያለሙበት ጊዜ ኃላፊነታቸውንና ተጠያቂነታቸውን አውቀው ወደ ትግበራ እንዲገቡ ለማድረግ ነው።

2) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ሶፍትዌር ለማልማት የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች በመቀበል ኃላፊነቱንና ተጠያቂነቱን ተገንዝቦ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ ለማድረግ ነው።

3) የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ሶፍትዌሮችን በሚያስለሙበት ጊዜ በድግግሞሽ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን የሀብት ብክነት ለመከላከልና ወጥነት ያለው አሰራር ለማስፈን ነው።

## ክፍል ሁለት

## የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 5. የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊነት

#### 1) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ ኃላፊነት

ሀ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ሶፍትዌሮችን ለማስለማት ጥያቄዎችን በሚያቀርቡበት ጊዜ የጥያቄዎችን አስፈላጊነት አጣርቶ ለሚኒ-ካቢኔ አቀርቦ በማፀደቅ ተገቢውን ግብረ-መልስ ለጠያቂው አካል ያቀርባል። ይህንን ሂደት በተመለከተ ቢሮው በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የማስፈፃም ስልጣን ተሰጥቶታል።

ለ) በስትሪንግ እና ቴክኒካል ኮሚቴ ውስጥ የሚሳተፉ ኃላፊዎችን እና ባለሙያዎችን የመመደብ ኃላፊነት ይኖረዋል።

### 6. የአስፈፃሚ አካላት ተግባር

#### 1) የሶፍትዌር ልማትና ፕሮጀክት ክትትል መምሪያ

ሀ) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ለመልማት በሂደት ላይ የሚገኙ ሶፍትዌሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተደራጅተው እንዲያዙ ማድረግ፣

ለ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማት እንዲለሙላቸው የሚፈልጓቸውን የሶፍትዌሮች አይነትና አስፈላጊነት የሚገልጽ ሰነድ ሲልኩ አስፈላጊውን የማጣራት ስራ ማከናዎን፣

ሐ) በቢጋር ዝግጅት ወቅት ባለሙያ በመመደብ ሶፍትዌሩ ከሚለማላቸው ቢሮዎች እና ተጠሪ ተቋማት ባለሙያዎች ጋር በጋራ መስራት፣

መ) የጨረታ ሰነድ ግምገማ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎችን መመደብ፣

ሠ) የለማው ሶፍትዌር የሙከራ ትግበራ በሚከናወንበት ወቅት ባለሙያ መመደብ፣

#### 2) የዳታቤዝና አፕልኬሽን አስተዳደር መምሪያ

ሀ) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ከአሁን በፊት የለሙ ሶፍትዌሮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተደራጅተው ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣

ለ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማት እንዲለሙላቸው የሚፈልጓቸውን የሶፍትዌሮች አይነትና አስፈላጊነት የሚገልጽ ሰነድ ሲልኩ አስፈላጊውን የማጣራት ስራ ማከናዎን፣

#### 3) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት

ሀ) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማት እንዲለማላቸው የሚፈልጓቸውን የሶፍቴዌር አይነቶች እና አስፈላጊነት የሚገልጽ ሰነድ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢር ማቅረብ፤

ለ) በቢጋር ዝግጅት ወቅት ባለሙያ በመመደብ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ ጋር በጋራ መስራት፤

ሐ) በስትሪንግ እና ቴክኒካል ኮሚቴ ውስጥ የሚሳተፉ ኃላፊዎችን እና ባለሙያዎችን መመደብ፤

መ) የጨረታ ሰነድ ግምገማ ላይ የሚሳተፉ እና የግዢ ሂደቱን የሚከታተሉ ባለሙያዎችን መመደብ፤

ሠ) የለማው ሶፍትዌር የሙከራ ትግበራ በሚከናወንበት ወቅት ባለሙያ መመደብ እና አስፈላጊ ግብአቶችን ማሟላት፤

ረ) የለማውን ሶፍትዌር መረከብ ናቸው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሶፍትዌር ልማቱን በተመለከተ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

### 7. የሶፍትዌሩ መልማት አስፈላጊነት

ሶፍትዌር እንዲለማለት የጠየቀው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮ፣ ጽ/ቤት ወይም ተጠሪ ተቋም ስለሶፍትዌሩ አይነት እና አስፈላጊነት የሚያሳይ ሰነድ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ ያቀርባል፡፡ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ የሶፍትዌሩን አይነት፣ አስፈላጊነት፣ ከዚህ በፊት የለማ ወይም እየለማ አለመሆኑን እና አቅምን ያገናዘበ መሆኑን አጣርቶ ለሚኒስቴር አቅርቦ በማፀደግ የተገኘውን ውጤት መሠረት ያደረገ ግብረመልስ ለጠያቂው አካል ይሰጣል፡፡

### 8. የቢጋር /TOR/ ዝግጅት

ሶፍትዌሩ እንዲለማለት ከጠየቀው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮ፣ ጽ/ቤት ወይም ተጠሪ ተቋም እና ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ በተወጣጡ ባለሙያዎች በሚዋቀር ቡድን የሚፈለገው ቢጋር ይዘጋጃል፡፡

### 9. የመግባቢያ ሰነድ

ሶፍትዌሩን ለማልማት በህጋዊ መንገድ የተመረጠው ተቋም የሚያቀርበው የመግባቢያ ሰነድ በሚኒስቴር ከጸደቀ በኋላ የሶፍትዌር ልማቱን ሂደት የሚከታተል የቢሮ ወይም የመምሪያ

ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት ስትሪንግ ኮሚቴ እና ቴክኒካል ስራዎችን የሚከታተሉ ባለሙያዎችን በአባልነት ያካተተ ቴክኒካል ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

## 10. የፍላጎት ሰነድ እና የዲዛይን ሰነድ ላይ አስተያየት መስጠት

ሶፍትዌሩን የሚያስመማው ተቋም በሚያቀርበው የፍላጎት ሰነድ እና የሲስተም ዲዛይን ሰነድ መሠረት ቴክኒካል ኮሚቴው በወቅቱ ግብረ-መልስ በመስጠት ሰነዶች በሚፈለገው ደረጃ ተጠናቀው በሚኒ-ካቢኔ እንዲጸድቁ ይደረጋል፡፡

## 11. የሙከራ ትግበራ ማካሄድ

ሶፍትዌሩ ለምቶ የሙከራ ትግበራ በሚካሄድበት ጊዜ ሶፍትዌሩ ከሚለማለት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮ፣ ጽ/ቤት ወይም ተጠሪ ተቋም እና ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ የተወጣጡ ባለሙያዎች በጋራ የሙከራ ትግበራውን በማከናወን ሶፍትዌሩ በትክክል መስራቱ ይረጋገጣል፡፡

## 12. የሶፍትዌር ርክክብ ማድረግ

ሶፍትዌሩ እንዲለማለት የጠየቀው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮ፣ ጽ/ቤት ወይም ተጠሪ ተቋም የሶፍትዌሩ ርክክብ በሚከናወንበት ጊዜ በቢጋሩ፣ በመግባቢያ ሰነዱ እና በሌሎች የውል ሰነዶች ላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ መሟላታቸውን አረጋግጦ ቀሪ ክፍያዎችን በመክፈል ሶፍትዌሩን ይረከባል፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 13. የተከለከሉ ተግባራት

1) የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ ማረጋገጫ ሳያገኙ ሶፍትዌሮችን ማልማትም ሆነ ማስለማት አይችሉም፡፡
2) ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት የሚጠይቁትን የሶፍትዌር ልማት ማረጋገጫ ካለበቂ ምክንያት ማዘግየትም ሆነ መከልከል አይችልም፡፡
3) ይህን መመሪያ ተላልፎ ሶፍትዌር አልምቶ ቢገኝ እንደጥፋቱ ክብደት ታይቶ አግባብ ባለው ሕግ የመ/ቤቱ የሠራተኛ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 እና በሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 መሰረት በዲስፕሊን ጥፋቱ ይጠየቃል፡፡
4) ጥፋቱ በመ/ቤቱ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡

14. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

15. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም**

**የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**